# የተበደለ/የተጎሳቆለ እና የተተወ/ትኩረት የተነፈገው-የተነፈጋት ልጅ ማጤን እና ሪፖርት ማድረግ ዘወትር የሚቀርቡ የበጎ-ፈቃደኛ ጥያቄዎች የ– 20 በጀት ዓመት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎቻችንን ተሞክሮዎች ለማበልፀግ በት/ቤቶቻችን ለሚሰሩ በጎ-ፈቃደኞች ከፍ ያለ አክብሮት አለው። እንደማህበረሰብ፣ ተማሪዎቻችን የሚያድጉበት ሰላማዊ፣ አካባቢዎች መፍጠር የጋራ ሀላፊነታችን መሆኑን እንገነዘባለን። ለእነዚህ አዘውትረው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች(FAQs) የሚመለሱ መልሶች ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና እና የበፊት ታሪክ/ባክግራዉንድ ተፈላጊ ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ ነው።

አዘውትረው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ዶኩመንት ከሚከተሉት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም እና የተደገፈ ነው፦ Montgomery County Board of Education Policy JHC, Child Abuse and Neglect, Montgomery County Public Schools Regulation JHC-RA, Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect, and Montgomery County Public Schools Regulation IRB-RA, Volunteers in Schools. በጉስቁልና እና በቸልተኝነት የተተው-የተተወች ልጅ ድረ-ገጽ "Child Abuse and Neglect website" ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ https://www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect/

**የጎብኚ አስተዳደር ስርዓት፦**

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ1፦ ጎብኚዎች፣ በጎፈቃደኞችን ጨምሮ ትምህርት ቤት በሚደርሱበት ወቅት ምን ማድረግ አለባቸው?** | መ1፦ በተመደበው የት/ቤት ሠዓት፣ ጠቅላላ ጎብኚዎች፣ በጎፈቃደኞን ጨምሮ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የጎብኚዎች ማኔጅመንት ሲስተም/MCPS Visitor Management System (VMS) በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤቶች ሲገቡ መመዝገብ አለባቸው። |
| **ጥ2፦ የጎብኚዎች ማኔጅመንት ሲስተም/Visitor Management System (VMS) ምንድነው?** | መ2፦ VMS በስቴት ጾታዊ ጥቃት ሪኮርድ ያለበ(ባ)ትን ለማጣራት የጎብኚዎችን የመንጃ ፈቃድ ወይም ከስቴት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ ስካን ያደርጋል። VMS በተጨማሪ በት/ቤቱ ህንፃ ባሉበት ወቅት ሁልጊዜ መደረግ ያለበትን የሚለጠፍ የስም ባጅ ይሰራል። |

**ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና ተፈላጊ ነገሮች፦**

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ3፦ በጎፈቃደኞች በጉስቁልና እና በቸልተኝነት የተተወ(ች) ልጅን መገንዘብ እና ሪፖርት ስለማድረግ ለበጎፈቃደኞች እና ኮንትራክተሮች ስልጠናን መውሰድ ይኖርባቸዋል?** | መ3፦ አዎ። ትምህርት ቤቶችን እና ተማሪዎችን በመደበኛነት የሚረዱ በጎፈቃደኞች በጠቅላላ እና የመስክ ጉዞዎች ላይ የሚሳተፉ እንዲሁም ኮንትራክተሮች ሁሉ በቸልተኝነት ስለተተወ እና የተጎሣቆለ(ች) ልጅ መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ በአውታረ-መረብ የሚሰጥ ሞዱዩል መሙላት አለባቸው። ይህ የስልጠና አስፈላጊነት በትምህርት ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎችን በመደበኛነት በበጎ ፈቃደኝነት በሚረዱ ሁሉ ላይ ይሠራል። |
| **ጥ4፦ እኔ ይህንን ስልጠና እንዴት ለማግኘት እችላለሁ?** | መ4፦ በቸልተኝነት የተተወ(ች) እና የተጎሣቆለ(ች) ልጅ ድረ-ገጽ ላይ እዚህ ይገኛል። |
| **ጥ5፦ ማንኛውም ለትምህርት ቤት ድጋፍ የሚሰጥ/የምትሰጥ ሰው የስልጠና መስፈርቶቹን መሙላት አለበ(ባ)ት?** | መ5፦ የማህበረሰብ አባላት በሙሉ በዚህ አስፈላጊ እና ጠቃሚ ስልጠና ላይ እንዲሣተፉ ብናደፋፍርም፣ ለአሁኑ አስፈላጊ የሚሆነው በመደበኛነት ትምህርት ቤቶችን በመደገፍ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ይህንን በቸልተኝነት የተተወ(ች) እና በጉስቁልና ስለሚገኝ/ስለምትገኝ ልጅ ስልጠና እንዲወስዱ ትኩረት ይሰጣል። ቢሆንም፣ ይህ ግዴታ በት/ቤት ሰራተኛ አባሎች ቁጥጥር ስር በታላቅ ዝግጅቶች ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ወይም ለአንድ ወቅት ድርጊቶች በሚያግዙ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። የበጎ ፈቃደኝነት ስልጠና ማሟላት የማያስፈልጋቸው የእንቅስቃሴ-ተግባሮች የሚከተሉት ናቸው (ዝርዝሩ የተሟላ አይደለም)፦<br>የ MCPS ሰራተኛ የሚቆጣጠራቸው በመማርያ ክፍሎች እንግዳ ኣንባቢዎችና ተናጋሪዎች፤ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-የኮሌጅ መልማዮችና በጎፈቃደኞች በምልመላ ስራ ላይ ሲሆኑ እና በኮሌጅ በዓላት ጊዜ/college fairs<br>ክብረ በዓሉ ላይ የተገኙ ወይም የሚደግፉ (ለምሳሌ፦ የሠልፍ ትርኢት) ወይም ክፍል ውስጥ በተዘጋጀ ፓርቲ ደጋፊ የሆኑ ወላጅ/ሞግዚቶች ወይም ሌሎች ዘመዶች፣ እና በትልልቅ ሁነቶች-ዝግጅት ወላጅ/ሞግዚቶች አባሎች የቲኬት መሸጫ ልዩ ዋጋ እና መደብሮች |
| **ጥ6፦ የበጎፈቃደኛ ስልጠና የሚገኘው መቼ ነው?** | መ6፦ በጉስቁልና እና በቸልተኝነት ስለ ተተወ(ች) ልጅ ስልጠና በድረ-ገጽ ላይ እዚህ ይገኛል። |
| **ጥ7፦ እኔ MCPS ስልጠና በ 2016-2017፣ 2017-2018፣ ወይም በ 2018-2019 የትምህርት ዓመት ወስጄ ከሆነ፣ እንደገና ለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት መውሰድ ይኖርብኛል?** | መ7፦ አይደለም MCPS ባለፈው ዓመት የሰጠውን ስልጠና አንድ ግለሰብ ማጠናቀቁ(ቋ)ን የMCPS ሪኮርድ የሚያሣይ ከሆነ፣ ግለሰቡ(ቧ) ለ2019-2020 ተጨማሪ ስልጠና መውሰድ አይኖርበ(ባ)ትም። ስልጠናው የሚያስፈልገው ከበጀት ዓመት 17 የትምህርት ዓመት/FY17 school year* በኋላ በየሦስት ዓመቱ ነው። የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና ተወስዶ ከሆነ፦<br>2016-2017 በ2020-2021 መታደስ ኣለበት* |

| | |
|---|---|
| | 2017-2018 በ2020-2021 መታደስ ኣለበት<br>2018-2019 በ2021-2022 መታደስ ኣለበት |
| **ጥ8፡- በጎፈቃደኞች በሙሉ የስልጠና ሞዱሉን በድረ-ገጽ መሙላት አለባቸው?** | መ8፡- በጎፈቃደኞች በሙሉ ስልጠናውን "Abuse and Neglect webpage" ድረ-ገጽ ላይ መሙላት ይጠበቅባቸዋል ይህ አስፈላጊ ሁኔታ መጠናቀቁን የኤሌክትሮኒክ ማረጋገጫ እዚህ ማግኘት ይቻላል።<br><br>በጎፈቃደኛ "Child Abuse and Neglect" ስልጠና አሟልቶ/ታ ከሆነ፣ ስማቸው በ "myMCPS Volunteer/Contractor Completion Report" (under the compliance section) ሪፖርት ላይ ይሰፍራል።<br><br><br><br>በጎፈቃደኛ "Child Abuse and Neglect" ስልጠናውን ካላሟላ/ች ይህንን ለማሟላት አካውንት መክፈት ያስፈልጋል። ወላጆች ወይም ሞግዚቶች የ MCPS Parent Portal አካውንት መጠቀም ወይም መክፈት ይችላሉ፣ ነገር ግን ወላጆች ያልሆኑት በዚህ link አካውንት ለመፍጠር ይችላሉ። ይህ ሪሶርስ/resource ወላጆች/ሞግዚቶች የ MCPS Parent Portal አካውንት እንዲከፍቱ ትምህርት ቤቶችን ይረዳል። አንዴ አካውንታቸውን ካገኙ በኋላ፣ ስልጠናውን ለማጠናቀቅ እና ስለማጠናቀቃቸውም በኮርስ ስልጠና ላይ ሪኮርድ ሊኖራቸው ይችላል። ከጁላይ 1ጀምሮ "Child Abuse and Neglect" ስለማጠናቀቃቸው 100% ኮርስ ውጤቶች ላይ ማረጋገጫ ይመዘገባል። ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ሊንክ ሪፖርቱን ለማግኘት ይችላሉ፣ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች ውጤታቸውን ለትምህርት ቤት ማቅረብ ካለባቸው በፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ወደ ኮርስ ስልጠና አካውንት ተመልሰው ሊያገኙት ይችላሉ። የዚህ አዲስ አሠራር ጥቅሙ እጥፍ ድርብ ነው፡- በጎፈቃደኞች ያጠናቀቁበትን መረጃ ሊጠፉባቸው አይችልም እና ወላጆች/ሞግዚቶች የ "MCPS Parent Portal" አካውንት እስከተጠቀሙ ድረስ፣ ከተማሪያቸው ጋር ስለሚገናኝ ያጠናቀቁበት መረጃ (በጎፈቃደኛ/ኮንትራክተር ያጠናቀቁበት ሪፖርት) በማናቸውም ምክንያት ትምህርት ቤቶችን ከሚዘወሩ/ከሚያንቀሳቅሱ ተማሪዎቻቸው ጋር ይመሣከራል። በዚህ በአዲሱ የሪፖርት መቅረጫ ምክንያት፣ ትምህርት ቤቶች ለበጎፈቃደኞቻቸው የግል ወይም አነስተኛ ቡድን ስልጠና ለመስጠት የድረ-ገጽ ሞዱል እንደሪሶርስ ግብአት የመጠቀም አማራጭ አይኖራቸውም። ወላጅ/ኣሳዳጊዎች በመገልገያዎች ተፈላጊነት ምክንያት በት/ቤታቸው ከመሳተፍ ኣይከለከሉም። ትምህርት ቤቶች፡- Office of Student and Family Support and Engagement (OSFSE) በ OSFSE@mcpsmd.org ለበጎፈቃደኞች የስልጠና ዳታቤዝ/የመረጃ ቋት ሪፖርቶች የሚሆን ግብአት፣ እና ማንኛውንም ልዩ የአኮሞዴሽን/special accommodation ጥያቄዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። |
| **ጥ9፡- የአካል ስንክልና ላለባቸው ስልጠና ለመሙላት "accommodations" የሚያስፈልገኝ ከሆነስ ምን ይደረጋል?** | መ9፡- ርእሰመምህራን እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የአካል ስንክልና ያለባቸውን ግለሰቦች በትምህርት ቤቶቻቸው እንደአግባብነቱ እና ከ OSFSE በመመካከር ማስተናገድ ይኖርባቸዋል። [A8 ይመልከቱ] |
| **ጥ10፡- የድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና በተለያዩ ቋንቋዎች ይሰጣል?** | መ10፡- አዎ  የድረ-ገጽ ስልጠናው በአሁኑ ወቅት በእንግሊዝኛ፣ ስፓንሽኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮርያንኛ፣ በአማርኛ እና በቬትናምኛ ይገኛል። |
| **ጥ11፡- በጎፈቃደኞች ስልጠና ማሟላታቸውን እንዴት እናውቃለን?** | መ11፡- በጎፈቃደኞች ስልጠና እንዳጠናቀቁ፣ ተሳትፎአቸው ሪኮርድ ስለሚደረግ በ MCPS ለመታየት ይችላል። አዲሱ አሠራር በ MCPS Parent Portal አካውንት ያስፈልጋል፣ ስለማጠናቀቃቸው ማረጋገጫ በ100% የኮርስ ውጤታቸው ላይ ይመዘገባል። ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ሊንክ ሪፖርቱን ለማግኘት ይችላሉ፣ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች ውጤታቸውን ለትምህርት ቤት ማቅረብ ካለባቸው በፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ወደ ኮርስ ስልጠና አካውንት ተመልሰው ሊያገኙት ይችላሉ። |
| **ጥ12፡- በጎፈቃደኞች ስልጠናውን ከወሰዱ፣ ከተማሪዎች ጋር ይሠራሉ?** | መ12፡- አዎ ት/ቤት ባዘጋጃቸው የተለያዩ መንገዶች በጎፈቃደኞች ትምህርት ቤትን ለመርዳት ይችላሉ። |
| **ጥ13፡- ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች የድረ-ገጽ ስልጠና መሙላት ይጠበቅባቸዋል?** | መ13፡- አይደለም ካፍቴሪያ ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች እንደመደበኛ በጎፈቃደኛ አይቆጠሩም እና በዚህ ወቅት የ MCPS ሠራተኞች ይቆጣጠሯቸዋል። |
| **ጥ14፡- ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪዎች በሚለቀቁበት** | መ14፡- አዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ት/ቤት በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች |

| | |
|---|---|
| **ወቅት ወይም በእረፍት ሠዓት የሚረዱ ከሆነ ስልጠና መውሰድ አለባቸው?** | ከተማሪዎች ጋር የሚሠሩ ወላጆች/ሞግዚቶች በትምህርት ቤት ውስጥ በጎፈቃደኝነት ከመጀመራቸው በፊት በድረ-ገጽ ስልጠና ማሟላት አለባቸው። |
| **ጥ15፦ ት/ቤትን የሚረዱ የ MCPS በጎ ፈቃደኛ - ተማሪዎች በድረ-ገጽ ላይ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | መ15፦ አይደለም በትምህርት ቤት እየረዱ ያሉ የ MCPS በጎፈቃደኛ-ተማሪዎች ሁልጊዜም በ MCPS ሠራተኛ አማካይነት ቁጥጥር ይደረጋል። |
| **ጥ16፦ ተማሪ መምህራን እና interns በድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | መ16፦ አዎ ተማሪ አስተማሪዎች እና interns "Child Abuse and Neglect" የግዴታ/mandatory ስልጠና እዚህ በድረ-ገጽ እንዲሞሉ ይጠበቅባቸዋል። |

**የጣት አሻራና የበፊት ታሪክ ማጣራት/ Background Check አስፈላጊነት/ግዴታዎች፦**

| ጥያቄ | መልስ |
|---|---|
| **ጥ17፦ ለበጎፈቃደኞች የበፊት ታሪካቸውን ማረጋገጫ መስፈርቶች/background check requirements ምንድናቸው?** | መ17፦ በሚከተሉት መደቦች/categories የሚሳተፉ በጎፈቃደኞች የጣት አሻራ እና የበፊት-ስነምግባር ማረጋገጫ መሙላት ይጠበቅባቸዋል፦<br>በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣<br>የ6ኛ ክፍል ከክፍል ውጭ የከባቢ ትምህርት ፕሮግራሞች (Outdoor Education) በማጀብ አብረው የሚሄዱ/chaperones፣<br>ከአካባቢ ውጭ እና/ወይም በምሽት የሚታደርበት የመስክ ጉዞዎች በጎ-ፈቃደኞች፣ እና ለረዥም ቀን ጉዞ የበጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ማጽደቅ የሚያስፈልገዉ። (ለምሳሌ፦ የጉዞ መነሻ ሠዓት በ MCPS ሥራ የሚጀመርበት ሠዓት እና/ወይም የመመለሻው ሠዓት ከ7:00 p.m በኋላ ከሆነ)<br><br>[ማሳሰቢያ -- በአንድ ቀን ከ 100 ማይሎች ያነሰ ጉዞዎችን የሚያደርጉ አትሌቶች/የስነ ጥበብ ተጓዦች በጠቅላላ የ "chaperone/volunteer" የጣት አሻራዎችን ወይም የበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ማሟላት አያስፈልጋቸውም።]<br><br>በስራ ላይ የሚገኙ የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ሕግ አስከባሪዎች በሥራ አቀጣጠር ምክንያት ያለፈ የወንጀል ማጣሪያ ያሟሉ እናም ከMCPS የበፊት ጥናት/ማረጋገጫ አይመለከታቸውም። ቢሆንም ግን፣ የተቀጠሩበትን እና የሥራ መታወቂያ ቁጥራቸውን ፎርም ጭምር ከኤጀንሲው ለማጣራት የጣት አሻራ ጽ/ቤትን በቁጥር፦ 301-279-3276 ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች ለሥራቸው (White House, a government agency, etc.) የጣት አሻራ ያላቸው በሙሉ፣ MCPS (ያለፈውን እና የወደፊት የወንጀል ድርጊቶችን) ሪፖርቶች ከኃላፊዎቹ ለመውሰድ እንዲችል በ MCPS ወይም American Identity Solutions (AIS) አማካይነት የጣት አሻራ መስጠት አለባቸው። |
| **ጥ18፦ በጎፈቃደኞች ስለበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ለማግኘት መሄድ ያለባቸው የት ነው እና ማጣሪያውን ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?** | መ18፦ የጣት አሻራ እና የበፊት-ስነምግባር ማጣራት ምናልባት በሚከተሉት ቦታዎች በቀጠሮ ለማግኘት ይቻላል፦<br><br>The Office of Human Resources Development/የሰብአዊ ኃይል እድገት ጽ/ቤት (OHRD)፣ የሚገኘውም፦<br>45 West Gude Drive, Rockville, Maryland 20850።<br>American Identity Solutions/የአሜሪካ ማንነት መፍትሄ (AIS)፣ የሚገኘውም፦<br>6701 Democracy Boulevard, Suite 110, Bethesda, Maryland 20817<br>12501 Prosperity Drive, Suite 200, Silver Spring, Maryland 20904<br>7361 Calhoun Place, Rockville, Maryland 20855<br>12800 Middlebrook Rd., Suite 112-B, Germantown, Maryland 20874, 301-383-9651<br>የበፊት ታሪክ የማጣራት ሂደት ለመጨረስ አራት ሳምንት አካባቢ ይወስዳል። |

| | |
|---|---|
| **ጥ19፡- ለበጎፈቃደኞች የበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ለማሟላት ወጪውን ማን ይከፍላል?** | መ19፡- የበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ የማድረግ ወጪ መሸፈን የበጎፈቃደኛ ኃላፊነት ነው። በ OHRD እና AIS ወጪው $52.25 ነው። እያንዳዱ ጉዳይ እየታየ፣ ወጪዎቹ የሚሸፈኑበትን መንገድ ት/ቤቶች ከበጎ-ፈቃደኞች ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ።<br>ከቤት ውጭ በመስክ ለሚሰጥ ትምህርት የሌሊት አጃቢዎች/chaperones የጣት አሻራ በ OHRD በኩል ከተፈፀመ ለአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ወጪ አይኖራቸውም።<br>በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣ በአትሌቲክ መምርያ በኩል እንደተዘጋጀው፣ የአለፈ ታሪክ ለማጣራት/background checks ክፍያውን ይቀጥላሉ። |
| **ጥ20፡- የ MCPS የበፊት ታሪክ ማጣራት/background checks ባለፈው አመት ከፈፀምኩ ሌላ የአለፈ ታሪክ ማጣራት ማድረግ አለብኝ ወይ?** | ጥ20፡- ወላጅ/ሞግዚት/የማህበረሰብ አባል ቀደም ሲል በ 2017-2018 ወይም በ 2018-2019 የትምህርት ዓመት የ"MCPS background check" ሂደት አሟልቶ/ታ ከሆነ፣ እኚህ ሰው በዚህ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ወቅት ድጋሚ መሙላት አይኖርባቸዉም። በአዲሱ የ "Federal RapBack Guidelines (Record of Arrest and Prosecutions BACK program)" ምክንያት ተፈላጊ መስፈርቶች ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው እና ይህ መረጃ በማሻሻል ሂደት ላይ ነው። ለወቅታዊ መረጃ እባክዎ ከ OHRD ይጠይቁ።] |
| **ጥ21፡- የት/ቤት ወላጅ መምህር (ተማሪ) ህብረት/Parent Teacher (Student) Association (PTA/PTSA) ከትምህርት-በኋላ እንቅስቃሴ፣ ማጎልመሻ ፕሮግራም፣ ወይም ሌላ ፕሮግራም ስፖንሰር ቢያደርጉ፣ የ MCPS ኮንትራክተሮችን የሚመለከተው የበፊት-ስነምግባር ማጣራት እና የጣት አሻራ የማቅረብ መስፈርት እነዚህንም ይመለከታቸዋል?** | መ21፡- የጣት አሻራ እና የበፊት-ስነምግባር ማጣራት የሚያስፈልጉት ትምህርት ቤት ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው ዝግጅቶች/ሁነቶች ብቻ ነው።<br>ከትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ በMCPS ገንዘብ ከተሰጠው ወይም ስፖንሰርድ ከሆነ ወይም MCPS የኮንትራቱ አካል ከሆነ (ይህም ማለት፣ የርእሰ መምህሩ/ሯ ፊርማ ኮንትራቱ ላይ ካለ)፣ ስልጠና ያስፈልጋል እናም የትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ አቅራቢዎች ቀጥተኛ፣ ቁጥጥር የሌለው መዳረሻ ወደ MCPS ተማሪዎች በ MCPS አገልግሎት መስጫ መዳረሻ ካለው የአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ይፈለጋል።<br>ኮንትራቱ በት/ቤት ስፖንሶርድ ካልሆነ እና ብቸኛ ስፖንሰር PTA/PTSA ወይም ሌላ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም Interagency Coordinating Board/የወኪል ድርጅቶች አስተባባሪ ቦርድ (ICB) ብቻ ከተደራጀ፣ MCPS የአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ወይም ስልጠና አይጠይቅም። ቢሆንም፣ PTA/PTSA ወይም ICB ለስራ ተቋራጮቻቸው ተጨማሪ ግዴታዎች ሊኖሯቸው ይችላል። |
| **ጥ22፡- በበጎ-ፈቃደኛነት  ለማገልገል ዝንባሌና ፍላጎት ያላቸው ፈቃድ ማግኘታቸውንና አለማግኘታቸውን ማን ይነግራቸዋል?** | መ22፡- በጎፈቃደኛ ለሚሆኑት የስቴት የበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ውጤት ብቻ በፖስታ ይደርሳቸዋል።  MCPS (OHRD) አንድ -በ- አንድ በማጣራት/ክትትል በማድረግ ስለ ጾታዊ ጥቃት የጥፋት ድርጊት፣ የልጆች ጾታዊ ጥቃት ጥፋት፣ እና የረብሸኝነት ወንጀል፣ እና ማናቸውንም የአደንዛዥ እፅ እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው-የተከለከሉ መዳኒቶችን የማሠራጨት ድርጊት ላይ የሚደረግ ተሳትፎን በፍጥነት ከበጎፈቃደኞች ጋር ክትትል ያደርጋል። OHRD ለበጎ-ፈቃደኛነት ታጭተው  የአለፈ ታሪክ ሲጣራ የተገኙ የወንጀል ዝርዝሮችን በሚመለከት በት/ቤት ከሚገኙ ሰራተኛ አባሎች ጋር አይጋራም። |
| **ጥ23፡- ስለ በጎ-ፈቃደኛ ስልጠናና የአለፈ ታሪክ ማጣራት/ background checks በሚመለከት ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን መጠየቅ አለብኝ?** | መ23፡- ስለበጎፈቃደኝነት መስፈርቶችን በተመለከተ ማናቸውም ጥያቄዎች ቢኖርዎት እባክዎን የእርስዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ። በተጨማሪ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ ምላሽ ያላገኙ ስጋቶችን በሚከተለው ኢ-ሜይል ወደ "Office of Student and Family Support and Engagement (OSFSE)" OSFSE@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር፡- 240-453-2426 ለማቅረብ ይቻላል። |
| **ጥ24፡- በ MCPS ጣቢያዎች ላይ ለሚሠሩ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞችን እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ይመለከታቸዋል?** | መ24፡- በ "dual enrollment program" የሚሠሩ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞች የወንጀል ማጣራት እና የጣት አሻራን ጭምር ለሥራ በሚቀጠሩበት ወቅት ያጠናቅቃሉ። ትምህርት ቤት ባሉበት ወቅት ከሞንትጎመሪ ኮሌጅ የተሰጣቸውን የመታወቂያ ባጅ በሚታይበት ሁኔታ ማድረግ አለባቸው። |
| **ጥ25፡- ለሞንትጎመሪ ካውንቲ -አስተዳደር (MCG) እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ሊተገበር ይችላል?** | መ25፡- ነርሶች እና የጤና ክፍል ቴክኒሻኖች የሚሣሰሉት የ MCG ሠራተኞች በሚቀጠሩበት ጊዜ የወንጀል ማጣራት ሥራ፣ እና የጣት አሻራ የሚሣሠሉትን ነገሮች ያጠናቅቃሉ። ትምህርት ቤት በሚሆኑበት ወቅት ከ MCG-የተሰጣቸውን የመታወቂያ ባጅ በሚታይ ሁኔታ ላይ ማድረግ አለባቸው። MCPS የወንጀል ማጣራት ሂደት ላጠናቀቁ ከትምህርት ፕሮግራሞች ጋር ለሚገናኙ የካውንቲ ሠራተኞች  በሙሉ የመታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል። |